# አባማ እና ኢትዮጵያ - ከተስፋ ማጣት ወደ መሪነት

ፕ/ር ዶናልድ ሌቪን

የሚገርም ዓመት! በኢትዮጵያና በዩናይትድ ስቴትስ የሚመሳሰሉ ትችቶችን እንሰማለን፤ በሁለቱም ሀገሮች የዋጋ ግሽበት ጉስቁልና እያመጣ ነው፣ በሀብታሞችና በድሆች መካከል ያለው ልዩነት ሰፍቷል፣ የታመሙ ሰዎች እንክብካቤ አጥተዋል፤ ሁኔታዎች እየተባባሱ እንጂ እየተሻሻሉ አልሄዱም። በሁለቱም ሀገሮች የሰብዓዊ መብት ጉዳይ አንገብጋቢ ሆኗል፤ ነጻጅና የኃይል አቅርቦት ውድና እጥረት ያለበት ሆኗል፤ ሚዲያው ለመደበቅ ተገዷል፤ የትምህርት ሽፋንና የትምህርት ቤቶች ብዛት፣ ከሕዝቡ ፍላጐት ጋር ሊመጣጠን አልቻለም። በተጨማሪም ሁለቱ ሀገራት በተሳሳተ ስሌትና ሃሣብ፣ የደህንነት ሥጋትን ለማስወገድ በሚል ሰበብ በሌላ ሀገር ያደረጉት ወረራ፣ ጋኔናዊ ጦስ ከፊታቸው ተደቅኗል፤ ተስፋ የማጣት ስሜት እንዲፈጠርብን እኒህ ከበቂ በላይ ናቸው።

በዩናይትድ ስቴትስ ፍስሐ እና ሐሴት፣ ስሜት፣ አዲስ ወኔ፣ ታላቅ ራዕይና የለውጥ ሃሣብ ከወዴት አሉ? እነዚህ የሚገኙት ብቃት ባለውና አብዛኛውን በሚያስማማ መልኩ፣ የሀገሪቱን ሕዝብ በአንድነት ይዞ፣ ሀገሪቱንና ሕዝቧን ያሽመደመዷትን ችግሮች መጋፈጥ በሚችል መሪ ዘንድ ነው። ለደጋፊዎቹና ለተከታዮቹ "ይህን ምርጫ ማሸነፍ ፋይዳው ለእኔ አይደለም፤ ይልቁንስ ፋይዳው ለእናንተ ነው" ብሎ በተናገረበት ጊዜ፣ አባማ አሜሪካንና ሕዝቧን ከተጋረጡባት ችግሮች ለመታደግ ያለውን ረጅምና ታላቅ ርዕይ አሳይቷል። ይህ የሚያመለክተው፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ነፃ እና ለሀገራቸውና ለወገናቸው ተቆርቋሪ የሆኑ አሜሪካውያንን አንድ ላይ በማሰባሰብ፣ ወደፊት ሊፈጠር የሚችለውን መልካም ነገር ነው። የኮመን ኮዝ (Common Cause) ፕሬዝዳንት ቦብ ኤድጋር እንደገለፀው፣ አሜሪካውያን "ስንጠብቀው የቆየነው መሪ ባለቤት ሆነናል።"

የባራክ አባማ ኃይል፣ አሜሪካና አሜሪካውያን በአስቸጋሪ ጊዜያት፣ አጥርተንና አርቀን እንድናስብ አድርገው፣ ካሳለፉንና ካቆዩን መሪዎቻችን ጋር አባማ ስለሚመሳሰል የመነጨ ነው። አባማ የሚያሽመደምድ የፍርሃት ውሽንፍርን (ሁለተኛው የዓለም ጦርነት) ካጠፉልን ከፍራንክሊን ሮዝቬልት፣ በከፍተኛ ዛቻና ማስፈራራት ሳይበገር፣ የእኩልነት ሃሣቡን ሲያራምድ ከነበረው ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ብሩህ ህልም ከሰጠን ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ እና የሚያጸጽት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቢያራምድም ተስፋ ያጣውን ሕዝብ፣ ሞራል እንደገና ካነሳሳው ከሮናልድ ሬጋን ጋር በእጅጉ ይመሳሰላል።

ልክ እንደ አሜሪካውያን ሁሉ፣ ኢትዮጵያውያንም በውድቀታቸው ጊዜያት፣ የመንፈስ ጽናት ለፈጠሩላቸውና የሆኗቸውን በርካታ ወገኖቻቸውን ያስታውሳሉ። ከወራሪ ጠላት ጋር ሲዋጋ የሞተውን አፄ ዮሐንስ፣ በዓለም መንግሥታት ማኅበር (League of nations) ስለ ሀገሩና፣ ስለ ሕዝቡ ነፃነት በመከራከር ገዝፎና ተልቆ የታየውን አፄ ኃይለሥላሴን፣ የኢጣሊያን ፋሺስታዊ ወረራ በጽናት ከተዋጉትና ከተቃወሙትም መካከል፣ እንደ ብላታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ፣ አቡነ ጴጥሮስ እና ጄ/ል ሙልጌታ

ቡሊ ያሉትን ያስባሉ። በዲሞክራሲ ባልታነፀ ሥርዓት፣ የዲሞክራሲን ሃሣብ ያራመደውን ክፍሌ ወዳጅ፣ የአንድን ብሔር የበላይነት በመቃወም፣ ለብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ፀንቶ የቆመውን አቶ ስዩ አብርሃን፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው የሕትመት ፕሮግራምና የሠላማዊ መፍትሔ ተቋም የከፈተውን አቶ ኤልያስ ወንድሙ፣ በከፍተኛ የተስፋ መንፈስ፣ አሰቃቂ እስራትን የተቋቋመችውን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣን እና በሺ የሚቆጠሩ ዜጐችን ከእስር የታደገውን ፓስተር ዳንኤል ገብረሥላሴ ያስታውሳሉ፣ ያደንቃሉም።

በአሁኑ ጊዜ ባራክ ኦባማ በአሜሪካ ለሚገኙ ባለሙብትና፣ የመምረጥ መብት ያላቸው ዜጐች እና እሱን መሰል ለሆኑ ተስፋ ፈንጣቂ ሰዎች፣ ለወቅቱ አጣብቂኝ ጉዳይና ችግር በአዲስ ኃይል፣ አዲስ መፍትሔ ለመፈለግ የድጋፍ ጥሪ ያቀርባል፣ ከመፍትሔዎቹ ሦስቱን እነሆ፡-

## የኃይል አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሣደግ

የቡሽ አስተዳደር የዓለም ሙቀት መጨመርን ይከዳል፤ ለአካባቢ እንክብካቤ ትኩረት አይሰጥም፤ ሣይንስን አያበረታታም፤ የነዳጅ ዘይትን በሥፋትና በቀጣይነት መጠቀም ያበረታታል። በተቃራኒው ባራክ ኦባማ የአካባቢ እንክብካቤን በጽኑ ይደግፋል፣ ለሣይንስ ተገቢውን ቦታ ይሠጣል እንዲሁም አማራጭ የኃይል ምንጭ ለማግኘት የሚደረግን ጥረት ይደግፋል። የኦባማ አዲሱ የኃይል አቅርቦትና አጠቃቀም ዕቅድ የነዳጅ ዘይት ፍጆታን መቀነስን፣ የአየር ብክለትን 80 በመቶ መቀነስን፣ አምስት ሚሊዮን የግሪን ኢነርጂ (Green Energy) ክፍት የሥራ ቦታዎች መፍጠርን እና አላቂ ያልሆነ (እንደገና መጠቀም የሚቻል) የኃይል ምንጭ ማስፋፋትን ያካተተ ነው።

## የውጭ ፖሊሲን መለወጥ

የኢራቅ መወረር በፖለቲካ፣ በሞራል፣ በኢኮኖሚ፣ በደህንነት፣ … ወዘተ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ውድቀት መሆኑን አሜሪካውያን ያምናሉ። የኢራቅ ወረራ ዓለም አቀፋዊ ጉዳይን፣ ጥሩዎችና መጥፎዎች ብሎ ከፋፍሎ ባስቀመጠ እና ነገሮችን በውል ባላገናዘበ አስተሳሰብ የተፈጸመ ነው። ጥሩዎች ነን ባዮች መጥፎ ባሏቸው ላይ የኃይል እርምጃ ለመውሰድ ባላቸው ጉጉት የፈፀሙት ነው። ፕሬዝዳንት ቡሽ በጃንዋሪ 2000 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ለፕሬዝዳንትነት በሚወዳደርበት ጊዜ “እኔ ሥልጣን ስይዝ (ጉዳዩ) እኛ እና እነርሱ ይሆናል። ዛሬ እነርሱ እነማን እንደሆኑ እርግጠኛ አይደለንም ነገር ግን እንዳሉ እናውቃለን” ብሎ ተናግሮ ነበር።

በዚያን ወቅት “ላልተወሰነ ጊዜ ሀገሪቱን ይዘን እንድንቆይ ያልታሰበና ያልታወቀ ወጭ እንድናወጣና ያልታወቀ ተጽዕኖ እንዲደርስብን እንገደዳለን” ሲል ኦባማ የኢራቅን ወረራ መቃወሙ፤ ለአሜሪካ ደህንነት የሚበጃትን አስተውሎ የሚወስን አዕምሮ እንዳለው የሚያመለክት ነው።

"ከጠረፎቻችን ባሻገር ያላችሁና በጉጉት የምትጠብቁን፣ ጉዳያችሁ ጉዳያችን ነው፤ ዕጣ ፈንታችሁም ዕጣ ፈንታችን ነው" ሲል ኦባማ ዓለማቀፋዊ አንድነትን መደገፉም የአስተዋይ አዕምሮው ምስክር ነው።

## የፖለቲካ ኃይልን እንደገና ማዋቀር

የቡሽ አስተዳደር በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች፣ ለአሜሪካ ዜጎች ያለውን ግዴለሽነት በገሃድ አሳይቷል። ይህ ግዴለሽነት የአደጋ ማስጠንቀቂያዎችን ሆን ብሎ ችላ ማለትን፣ ካተሪና የተሰኘው አውሎ ነፋስ ባስከተለው ጉዳት፣ ዜጎችን መልሶ አለማቋቋምን፣ ከሴፕቴምበር 9/11 በኋላ አሜሪካውያንን ለማኅበራዊ ግልጋሎት አለመቀስቀስ፣ አለማሳተፍን እና ሕገ መንግሥቱን በመጣስ፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትንና አሠራርን ማዳከምንና ማጣጣልን ይጨምራል። ከዚህ ሙሉ በሙሉ በተቃራኒ፣ ባራክ ኦባማ ለሕገመንግሥቱ ያለው የፀና ታማኝነት ከበቂ በላይ በቺካጐ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ስለ ሕገመንግሥት ሕግ በማስተማር እና የቡሽ አስተዳደር የፍትህ ሚኒስቴርን (Department of Justice) ፖለቲካዊ መስመርና ገጽታ እንዲኖረው ያደረገውን ጥረት ለመቀልበስ በጽኑ በመታገሉ ተመስክሯል። የኦባማ ዕቅድ የአሜሪካን መንግሥት፣ የፖለቲካ ኃይል በብሔራዊና ማኅበረሰባዊ ግልጋሎት ላይ ማዋል ነው። ኦባማ የዜጐችን አስተያየት በማድመጥና ምላሽ በመስጠት የካበተ ልምድ አለው፤ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ ፕሬስ መንግሥትን ሳንሱር እንደሚያደርግ እንጂ መንግሥት ፕሬስን ሳንሱር እንደማያደርግ በሚገባ ያውቃል።

## ጥሪ ለኢትዮጵያውያን

የኢትዮጵያ አሜሪካውያን ኦባማን መደገፍ እንዳለበት የተለያዩ ምክንያቶችን ይነግሩኛል፤ እንደ ሌሎች አሜሪካውያን ሁሉ፣ የኢትዮጵያ አሜሪካውያንም በኦባማ መጠነ ሠፊ የፖሊሲ ዕቅዶች ላይ የተመሠረተ ተስፋ አላቸው። ኦባማ ለአሜሪካ ያስቀመጣቸው አዳዲስ የለውጥ አቅጣጫዎችና የገባቸው ቃል ኪዳኖችም፣ አሜሪካ ለኢትዮጵያ የወደፊት መለወጥ አርአያና ሞዴል እንድትሆን ሊያደርግ እንደሚችልም ተገንዝበዋል። አብዛኛዎቹ ደግሞ የኦባማ አስተዳደር፣ አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድና በኢትዮጵያ ያላትን ፖሊሲ በማስተካከል፣ ገንቢ አቅጣጫ እንዲይዝ ያደርጋል የሚል ተስፋ አላቸው። ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ጨምሮ ከኦባማ አካባቢን የማይበክል የኃይል (Green Energy) በኢትዮጵያ መስፋፋትና ብሎም እንደ ምሥራቅና ምዕራብ እስያ ሀገሮች የታየውን ዓይነት የኢንዱስትሪ እመርታ እንደምታስመዘግብ፣ ከኦባማ ቃልኪዳን ተስፋ አላቸው። ይህ ደግሞ አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠው ድጋፍና ዕርዳታ ከተለመደው የሲራቡ ማጉረስ ዕርዳታና ሚዛናዊ ያልሆነ ካፒታል ኢንቨስትመንት ወደ ሶላር ጂኦተርማል በየአካባቢው የማመንጨትና የመጠቀም ሂደት ይሸጋገራል ማለት ነው። በርካታ ኢትዮጵያውያን ከኦባማ ፖሊሲዎችና ቃል ኪዳኖች ኢትዮጵያ

በሶማሊያ የምታደርገውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ አቁማ፣ በአንፃሩ ገርማሜ ንዋይ እንዳደረገው ሁሉ፣ የኦጋዴንን ነዋሪዎች ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ክፍል ጋር የሚያስተሳስሩበትና ኑሮአቸውን የሚቀይር አገልግሎት ላይ ታተኩራለች የሚል ተስፋ አላቸው።

የኦባማ ፖሊሲና የትኩረት አቅጣጫ፣ አሜሪካ በምሥራቅ በአፍሪካ የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች፣ በፀረ-ሽብር እና የጠመንጃ ቃታ በመሳብ ላይ ብቻ እንዳያተኩር ያደርጋል። ይህንን ለውጥ የአሜሪካ የቀድሞው አምባሣደር ዴቪድ ሺን እና የቀድሞዋ ጉዳይ አስፈፃሚ ቪኪ ሃድልስተን የሚደግፉትና የሚያስተጋቡት ነበር። ሰብዓዊ መብትን በማስጠበቅና ዜጐችን ለማኅበራዊ ግልጋሎት በመቀስቀስና በማሳተፍ ረገድ፣ ኦባማ ያለው አቋም ለኢትዮጵያ በማያሻማ መልኩ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ታችኛውን የኅብረተሰብ ክፍል በማጠናከርና የሙብት ባለቤት በማድረግ የለውጥ ምዕራፍ ይከፍታልና ነው። የኦባማ ፖሊሲ በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስና ነፃ ሚዲያ በተጠናከረ መንገድ የሚንቀሳቀሱበትን ዕድልም ያሰፋል፣ ያመቻቻል። ይህ ደግሞ የሕዝቡን ድምጽ በማስተጋባት፣ ሰብዓዊ መብቶችን በማስጠበቅና ለፖለቲካ ችግሮች ሠላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ የማፈላለግ አቅምን ያጐለብታል። ኦባማ ያስቀመጠው የውድድር መፈክር፣ በአገር ቤትም ሆነ በአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የሚመለከትና ኢትዮጵያንም ወደ ጥሩ መንገድ የሚመልስ ነው። አዎ! እንችላለን፤ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ለኦባማ ከመቆም የተሻለ ምን መንገድ አለ? እንዲያውም ከአፍሪካ ቀንድ ጐረቤቶቻችሁ ጋር በአንድነት አዲስ የድጋፍ ቡድን ፍጠሩ፤ የሱዳን፣ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ እና ሶማሊያ (SEEDS) ለኦባማ የሚል ቡድን ለምን አይኖርም?!